# ሠንደቅ ዓላማችን

ይውለብለብ፤ ይውለብለብ፤ ይውለብለብ በአገራችን፤
ይተከል ይርገብገብ ይርገብገብ በሰውነታችን፤
ከትውልድ ተላልፎ የተረከብነው ሰንደቅ ዓላማችን።

አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን፤
የነፃ አርማ የአእምሮ እረፍታችን፤
የልባችን ደስታ ታሪክ መስካሪያችን፤
በትውልድ ከትውልድ የትውልድ ሀብታችን፤
የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ምልክታችን፤
ታሪክን ወግን ወኔንና ክብርን መዝጋቢያችን፤
የሁሉ ኢትዮጵያዊ የጋራ ሀብታችን፤
የመንፈሳችን እረፍት ፍራሽ ድልዳላችን፤
የፍቅራችን ግለት ፍሙ ሙቀታችን፤
የማይሸጥ የማይለወጥ የአገር ውርሳችን፤
ከወርቅ ከአልማዝ ይከብራል ሰንደቅ ዓላማችን፤
ከፀሃይ ያበራል ይህ ድንቁ ቅርሳችን፤
ያከበሩትን ያሞቃል የኛ መለዮአችን፤
በየ አህጉሩ ላለነው ግርማ ሞገሳችን፤
የአንድነታችን ማሰሪያ ነው ሰንሰለታችን፤
መሐተባችን ሆኖ የእምነት ክታባችን፤
በሰው አይበጠስም ምን ቢዝል ገላችን።

ይውለብለብ ይውለብለብ ይውለብለብ በአገራችን፤
ይተከል ይርገብገብ ይርገብገብ በሰውነታችን፤
ከትውልድ ተላልፎ የተረከብነው ሰንደቅ ዓላማችን፤
ማንም ሊወስደው አይችልም ነቅሎ ከልባችን!!!

ከ ኒኒ ለገሰ